# 3ኛው ሀገር አቀፍ የሴቶች ጨዋታዎች የአትሌቲክስ ውድድር

# ሕግና ደንብ

# የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

የካቲት 22- 26/2011 ዓ.ም.
ጅግጅጋ

# የ3ኛው ሀገር አቀፍ የሴቶች ጨዋታዎች የአትሌቲክስ ውድድር
# ሕግና ደንብ አጠቃላይ መረጃ

- የውድድሩ ቀን፡-  ከየካቲት 22-26/2011 ዓ.ም.
- የውድድሩ ቦታ፡-  ጅግጅጋ
- የውድድሩ ተሳታፊዎች፡-  ክልልና ከ/አስተዳደሮች
- አዘጋጅ፡-  የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

## አድራሻ

- ፖ.ሣ.ቁ  13336
- ፋክስ  251-11-6450879
- ኢ-ሜል  eth@mf.iaaf.org
- Website  www.eaf.org.et
- ☎  251-11-6479579
  251-11-6479676
  251-11-6479596
  251-11-6479131
  ***ጉርድ ሾላ***
  ***አዲስ አበባ***

## ጥቅል ኘሮግራም

- *የካቲት 21/2011 ዓ.ም. የቴክኒክ ስብሰባ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት በጅግጅጋ ስታድየም*
- *ከየካቲት 22 እስከ የካቲት 26/2011 ዓ.ም. ውድድሩ የሚካሄድበት ቀን፤*

# የ3ኛው ሀገር አቀፍ የሴቶች ጨዋታዎች የአትሌቲክስ ውድድር
# ሕግና ደንብ

<u>ዓላማ</u> ፡ -

1. ሴቶች በስፖርቱ ዘርፍ ቀጥተኛ ተሳትፎ እና እኩል ተጠቃሚነት መርህን በየደረጃው ተግባራዊ በማድረግ፤ የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ውጤታማነት ለማረጋገጥ፤
2. ተተኪዎችን ለማፍራት፤

## *አንቀጽ አንድ*

## *አጠቃላይ የውድድሩ ደንብ*

1. **የውድድሩ መጠሪያ፡-** ይህ ውድድር 3ኛው ሀገር አቀፍ የሴቶች ጨዋታዎች አትሌቲክስ ውድድር ተብሎ ይጠራል፡፡
2. **ውድድሩ የሚመራው፡-** በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንና በIAAF የውድድር ህግና ደንብ መሠረት ይመራል፡፡
3. **ውድድሩን በበላይነት የሚመራ አካል፡-** የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ስፖርት ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ይሆናሉ፡፡
4. **የውድድሩ አግባብነት፡-** በአንድ የውድድር ተግባር ሁለት ክልሎች/ ከተማ አስተዳደሮች፣ ሦስት እና ከሦስት በላይ ተሳታፊ አትሌት ተመዝግበው ከቀረቡ ውድድሩ ይካሄዳል ከዚያ በታች ከሆነ ውድድሩ አይካሄድም
   - ውድድሩ በዘጠኙ ክልሎች እና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች መካከል ይካሄዳል፡፡
   - የውድድሩ አሸናፊ የሚለየው በሜዳሊያ (ወርቅ፣ ብርና ነሐስ) ብልጫ ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ ሁለት*

## *የውድድሩ ቀን፣ ቦታና ሰዓት*

3ኛው ሀገር አቀፍ የሴቶች ጨዋታዎች የአትሌቲክስ ውድድር ከየካቲት 22 እስከ የካቲት 26/2011 ዓ.ም. ብ/ክ/መንግስት ጅግጅጋ ከተማ ዘወትር ከጠዋቱ 2፡00 ጀምሮ ይካሄዳል፡፡

## *አንቀጽ ሦስት*

## *የውድድሩ አይነቶች*

3ኛው ሀገር አቀፍ የሴቶች የአትሌቲክስ ውድድር የሚደረገው ከዚህ በታች በተገለፀው የውድድር ተግባራት ይሆናል፡፡

1. 100 ሜትር
2. 200 ሜትር
3. 400 ሜትር
4. 800 ሜትር
5. 1500 ሜትር
6. 3000 ሜትር
7. 5000 ሜትር
8. 4X100 ሜትር
9. 4X400 ሜትር
10. አሎሎ ውርወራ
11. ጦር ውርወራ
12. ርዝመት ዝላይ
13. ከፍታ ዝላይ

## አንቀጽ አራት

## የተወዳዳሪዎች ተሳትፎ

1. አንድ ቡድን በየውድደር ተግባሩ /ኢቬንት/ አራት አትሌቶች ማስመዝገብ ይችላል፡፡ ከተመዘገቡት ውስጥ መወዳደር የሚችሉት ሦስቱ ብቻ ናቸው፡፡
2. አንድ አትሌት በሦስት የግል እና በአንድ የቡድን ኢቬንት ማሳተፍ ይችላል፡፡

## አንቀጽ አምስት

## ዕድሜ

በ3ኛው ሀገር አቀፍ የሴቶች ጨዋታዎች አትሌቲክስ ውድድር የሚሳተፉ ሴቶች ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ /በ1993/ የተወለዱ መሆን አለበት፡፡

## አንቀጽ ስድስት

## ምዝገባ

በ3ኛው ሀገር አቀፍ የሴቶች ጨዋታዎች አትሌቲክስ ውድድር የተሳታፊዎች የተወዳዳሪዎች ምዝገባ የሚካሄደው ከየካቲት 1-11/2011 ዓ.ም. ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ስፖርት ኮሚሽን ለምዝገባ የሚላከው ኮፒ እና በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጽ/ቤት ይዞ በመቅረብ ወይም በመላክ ከጠዋቱ 2፡30 ሰዓት እስከ ምሽቱ 11፡00 ሰዓት ድረስ ይሆናል፡፡ በዚህ የጊዜ ገደብ ያልተመዘገበ ክልል/ከተማ አስተዳደር የካቲት 12/2011 ዓ.ም ብር 300.00/ሦስት መቶ ብር/ በመክፈል ይመዘገባል፡፡

## አንቀጽ ሰባት

## የተወዳዳሪ ቅያሪ

ማንኛውም ቡድን በየውድድር ተግባሩ የተወዳዳሪ ለውጥ ማድረግ የሚችለው ከውድድሩ በፊት ዘወትር እስከ ቀኑ 5፡00 ለውድድሩ ከተመዘገቡት አትሌቶች ውስጥ ብቻ ነው፡፡ የተወዳዳሪዎች ቅያሪ ማድረግ የሚቻለው በየውድድር ምድቡ ከተመዘገቡት አትሌቶች ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ ስምንት

## ስለተገቢነት

1. **በ3ኛ ሀገር አቀፍ የሴቶች ጨዋታዎች አትሌቲክስ የሚሳተፉ፤**
   - በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ውስጥ በፊት ጀምሮ የኖሩ፤
   - በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ በሚከናወኑ ውድድር የተሳተፉ ሴቶች መሆን አለባቸው፡፡
2. በ3ኛው ሀገር አቀፍ የሴቶች ጨዋታዎች አትሌቲክስ ውድድር የማይሳተፉ፡-
   - የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ አትሌቶች፤
   - የጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሠልጠኛ ማዕከል አትሌቶች፤
   - የአራቱ የአትሌቲክስ ማሠልጠኛ ማዕከላት በአሁኑ ሰዓት እየሰለጠኑ ያሉ አትሌቶች፤
     1. በኦሮሚያ በቆጂ ማዕከል፤
     2. በደቡብ ሕዝቦች ሀገረ-ሠላም ማዕከል፤
     3. በትግራይ የማይጨው ማዕከል፤
     4. በአማራ ደብረ ብርሃን ማዕከል፤

- በታዳጊዎች አትሌቲክስ ስልጠና ፕሮጀክት ውስጥ ታቅፈው መረጃቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ቋት ውስጥ ያሉ ስፖርተኞች፤
- ከ1ኛ እስከ 6ኛው በተደረጉ የመላው የኢትዮጵያ ጨዋታዎች ላይ የተሳፉ አትሌቶች፤
- በ1ኛው እና 2ኛው ሀገር አቀፍ ተማሪዎች ስፖርት ጨዋታዎች የተሳተፉ፤
- በ1ኛው ሀገር አቀፍ ሴቶች ስፖርት ጨዋታ የተሳተፉ፤
- በማንኛውም አገር አቀፍ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተሳተፉ ተማሪዎች፤
- ከ1ኛ እስከ 5ኛው አገር አቀፍ የታዳጊዎች አትሌቲክስ ስልጠና ፕሮጀክት የተሳተፉ፤
- ከዚህ በፊት በስፖርት ስነ-ምግባር  የተከሰሰ ወይም ተከሰው ውሳኔ ያልተሰጠባቸው፤
- በማንኛውም ጊዜ በብሔራዊ ቡድን ተመርጠው የስልጠና ዕድል ያገኙ፤
- የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ባዘጋጃቸው ሻምፒዮናዎች የተሳተፉ፤
- በውጭ ሀገር ውድድሮች በግልም ሆነ ሀገርን በመወከል የተሳተፉ አትሌቶች፤

## *አንቀጽ ዘጠኝ*

## *በስም ጥሪ ቦታ በሰዓት መገኘት*

ማንኛውም ተወዳዳሪ ውድድሩ ከመጀመሩ ቢያንስ ከ45 ደቂቃ በፊት በስም ጥሪ ቦታ በመገኘት ለውድድሩ ዝግጁ መሆኑን ለስም ጠሪ ዳኞች ማሳወቅ ይጠበቅበታል፡፡ በስም ጥሪ ቦታ ላይ ተገኝቶ ስሙን ለስም ጠሪ ዳኞች ያላሳወቀ አትሌት በውድደሩ ላይ መካፈል አይችልም፡፡ ተካፍሎ ቢገኝ ውጤት ተቀባይነት የለውም፤

## *አንቀጽ አሥር*

## *የተወዳዳሪ ቴሴራ*

አንድ አትሌት የክልሉን/ከተማ አስተዳደሩን ተወዳደሪ መሆኑን የሚገልጽ የታደሰ ቴሴራ ይዞ ለውድድር መቅረብ አለበት፡፡ ቴሴራው ያልተሰረዘና ያልተደለዘ ሆኖ የተወዳዳሪውን ሙሉ መረጃ መያዝ አለበት፡፡

## *አንቀጽ አሥራ አንድ*

## *የአትሌቱ ጤንነት*

በውድድሩ ተካፋይ የሚሆን አትሌት ጤናው የተሟላ መሆን አለበት፤ የጤና ችግር ያለበት አትሌት ተሰልፎ ቢገኝና ጉዳት ቢደርስበት ተጠያቂ የሚሆነው እራሱ ክልሉ/ከተማ አስተዳድሩ እና አትሌቱ ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ አሰራ ሁለት*

## *ውጤትን ስለመግለጽ*

1. የውድድር ውጤቶች ለተወዳዳሪዎችና ለቡድኖች ወዲያውኑ በአስተዋዋቂና በኮሙኒኬ ይገለፃል፡፡
2. በተገለጹት ውጤቶች ላይ ስህተቶች ካሉ ወዲያውኑ የቡድን መሪው/አሠልጣኝ የውድድሩ ቴክኒካል መረጃ ክፍል (TIC) በመቅረብ የማስተካከያ ጥያቄ ማቅረብ ይቻላል፡፡
3. ከውድድሩ ቴክኒካል መረጃ ክፍል (TIC) የውድድሩን ውጤት ይፋ ሳይደረግ ውጤቱን ለህዝብ መግለጽ የተከለከለ ነው፡፡

## *አንቀጽ አስራ ሦስት*
## *ክስና ይግባኝ ስለማቅረብ*

1. የአትሌት ተገቢነት የክስ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው ውድድሩ ከመጀመሩ ቢያንስ ከ1 ሰዓት በፊት ነው፡፡
2. የውድድር ውጤቶችን ወይም የውድድር ተግባር ሁኔታን በተመለከተ የክስ ጥያቄ የሚቀርበው ውጤቱ ይፋ በሆነ በ30 ደቂቃ ጊዜ ውስጥ ነው፡፡
3. ማንኛውም የክስ ጥያቄ መጀመሪያ የሚቀርበው ለውድድሩ ዳኛ (refree) በቃል በአትሌቱ፣ በአሠልጣኙ ወይም በቡድን መሪው አማካይነት ሊሆን ይችላል፡፡ የውድድር ዳኛው ውሳኔ መስጠት ወይም ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4. በዳኛው ውሳኔ ያልተስማማ አካል በጽሑፍ ከብር 1000.00 (አንድ ሺ ብር) ጋር ለክስ ሰሚ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡ በፌዴሬሽኑ ክስ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ያልተስማማ ቡድን፣ በፌዴራል ደረጃ ለተዋቀረው የውድድር ሥነ-ሥርዓትና ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ብር 1,500.00 (አንድ ሺ  አምስት መቶ ብር) በማስያዝ ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የቀረበው ቅሬታ ትክክል ሆኖ ከተገኘ የተያዘው ብር ተመላሽ ይሆናል፡፡ ይግባኙ ተቀባይነት ካላገኘ የተያዘው 1500/አንድ ሺ አምስት መቶ/ ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ገቢ ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ አስራ አራት*
## *አለባበስ*

ማንኛውም ተወዳዳሪ የክልሉን ወይም የከተማ አስተዳደሩን መለያ የሆነውን የስፖርት ትጥቅ ለብሶ ለውድድር መቅረብ አለበት፤ መለያ ለብሶ ያልቀረበ ተወዳዳሪ መወዳደር አይችልም፤

## *አንቀጽ አስራ አምስት*
## *የመወዳደሪያ መሮጫ ቁጥር*

ማንኛውም ተወዳዳሪ አትሌት የመወዳደሪያ ቁጥር ሊኖረው ይገባል፣ ቁጥሩ የሚለጠፈው ግልጽ ሆኖ በሚታይ ቦታ በደረትና በጀርባ ላይ ነው፡፡ የከፍታ ዝላይ ተወዳዳሪዎች አንድ የመወዳደሪያ ቁጥር ብቻ በደረት ወይም ከጀርባ ላይ ለጥፎ መወዳደር ይችላል፡፡ በሪሌ ውድድር አትሌቱ የክልሉን ከተማ አስተዳደሩን ስም የሚገልጽ ጽሑፍ በደረቱ ላይ መለጠፍ አለበት፡፡

## *አንቀጽ አስራ ስድስት*
## *ሽልማት*

በእያንዳንዱ የውድድር ተግባር ከ1ኛ - 3ኛ ለሚመጡ አትሌቶች የወርቅ፣ የብርና የነሐስ ሜዳሊያ ሽልማት ይሰጣል፡፡ ለሪሌ ተወዳዳሪዎች 1ኛ ለሚወጡ አራት የወርቅ ሜዳሊያ፣ 2ኛ ለሚወጡ አራት የብር ሜዳሊያ ፣ 3ኛ ለሚወጡ አራት የነሐስ ሜዳሊያ ይሰጣል፡፡ ነገር ግን በፌዴራል ወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን አውራ ደንብ አንቀጽ ሃያ ሁለት መሠረት የሚቆጠር የሜዳሊያ ቁጥር በአሸነፉት ቅደም ተከተል መሠረት 1 ወርቅ፣ 1 ብር እና 1 ነሐስ ብቻ ለአሸናፊዎቹ ይመዘገባል፡፡

ማንኛውም ተወዳዳሪ ለሽልማት ሲቀርብ የክልሉን/ከ/አስተዳደሩን ማሊያ መልበስ ይኖርባታል፡፡ ይህ ካልሆነ ሽልማቱ አይሰጣትም፡፡

## *አንቀጽ አስራ ሰባት*

## *የሥነ-ሥርዓት ጉድለት*

ማንኛውም ተወዳዳሪ፣ አሰልጣኝ፣ የቡድን መሪ፣ ወጌሻ ወይም ሌሎች የቡድን አባላት ውድድሩ በሚከናወንበት ወቅት የሥነ-ሥርዓት ጉድለት ካሣዩና ውድድሩን በሚመሩ ዳኞች ወይም የውድድር አዘጋጆች ሪፖርት ቀርቦ ጥፋቱ ከተረጋገጠ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሕግና ደንብ መሠት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ አስራ ስምንት*

## *የቴክኒካል ስብሰባ*

የቴክኒካል ስብሰባ የካቲት 21/2011 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ጀምሮ ሶማሌ ብ/ክ/መንግስት በጅግጅጋ ስቴድየም ይካሄዳል፡፡

# 3ኛው አገር አቀፍ የሴቶች አትሌቲክስ ውድድር ኘሮግራም

## 1ኛ ቀን የካቲት 22/2011 ዓ.ም. ዓርብ/ጠዋት/

| ተ.ቁ. | ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የተግባሩ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 3:00 | አሎሎ ውርወራ | ሴት | ፍፃሜ |
| 2 | 3:10 | 100 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 3 | 3:40 | 400 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 4 | 4:10 | 800 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 5 | 4:40 | 5000 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 6 | 5:10 | 100 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 7 | 5:30 | 400 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 8 | 5:50 | አሎሎ | ሴት | ሽልማት |
| 9 | 6:00 | 5000 ሜትር | ሴት | ሽልማት |

## 2ኛ ቀን የካቲት 23/2011 ዓ.ም. ቅዳሜ /ጠዋት/

| ተ.ቁ. | ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የተግባሩ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 3:00 | ርዝመት ዝላይ | ሴት | ፍፃሜ |
| 2. | 3:15 | 800 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 3. | 3:35 | 100 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 4. | 4:00 | 4X400 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 5. | 4:20 | 3000 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 6. | 5:00 | ርዝመት ዝላይ | ሴት | ሽልማት |

## 3ኛ የካቲት 24/2011 ዓ.ም. እሁድ /ጠዋት/

| ተ.ቁ. | ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የተግባሩ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 3:00 | ጦር ውርወራ | ሴት | ፍፃሜ |
| 2. | 3:15 | 800 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 3. | 3:30 | 100 ሜተር | ሴት | ፍፃሜ |
| 4. | 3:45 | 4X400 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 5. | 4:00 | ጦር ውርወራ | ሴት | ሽልማት |
| 6. | 4:30 | 800 ሜትር | ሴት | ሽልማት |
| 7. | 4:50 | 100 ሜትር | ሴት | ሽልማት |
| 8. | 5:20 | 4X400 ሜትር | ሴት | ሽልማት |

# 2ኛው አገር አቀፍ የሴቶች አትሌቲክስ ውድድር ፕሮግራም

## 4ኛ ቀን የካቲት 25/2011 ዓ.ም. ሰኞ /ጠዋት/

| ተ.ቁ. | ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የተግባሩ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 3:00 | 200 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 2. | 3:30 | 400 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 3. | 4:00 | 1500 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 4. | 4:30 | 4 X100 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 5. | 4:50 | 400 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 6. | 5:20 | 200 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 7. | 5:40 | 3000 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |

## 5ኛ ቀን የካቲት 26/2011 ዓ.ም. ማክሰኞ /ጠዋት

| ተ.ቁ. | ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የተግባሩ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 3:00 | ከፍታ ዝላይ | ሴት | ፍፃሜ |
| 2. | 3:05 | 1500 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 3. | 3:20 | 200 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 4. | 3:35 | 400 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 5. | 3:50 | 4 X100 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 6. | 4:15 | 1500 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 7. | 4:05 | ከፍታ ዝላይ | ሴት | ሽልማት |
| 8. | 4:20 | 200 ሜትር | ሴት | ሽልማት |
| 9. | 4:35 | 400 ሜትር | ሴት | ሽልማት |
| 10. | 4:40 | 4 X100 | ሴት | ሽልማት |

**ማሳሰቢያ፡** - የውድድሩ ፕሮግራም እንደአስፈላጊነቱ ሊቀየር ወይም ሊሻሻል ይችላል፡፡

*የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን*